DANIEL FIKADU LAW OFFICE https://t.me/lawethiopiacomment

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ.230189
ጥቅምት 4 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡-. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነዓ ቂጣታ
ፈይሳ ወርቁ
ደጀኔ አያንሳ
ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- አቶ አብዱ ኤዳ -ቀርበዋል
ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዙሌይካ አዩብ- ቀርበዋል
ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የልጆች ቀለብና የግራ ቀኙ ጊዜያዊ የመኖሪያ ቤት የሚመለከት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ተጠሪ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር አመልካች፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት ወ/ሮ አብዲያ የሱፍ እና አቶ ጃቢር አብዱ የሥር ጣልቃ ገቦች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.224677 በ23/10/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ለግራ ቀኛችን አራት ልጆች የተወሰነዉ 20000 (ሀያ ሺህ) ብር ቀለብ ተሻሽሎ እንዲጨመርልኝ በማለት የጠየቁ ሲሆን፤ የአሁን አመልካች በበኩላቸዉ ደግሞ የልጆቹ ቀለብ መጠን እንዲቀነስልኝ በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በመስማት ጉዳዩን በመመርመር ባሳለፈዉ ዉሳኔ ለግራ ቀኙ አራት ልጆች የአሁን አመልካች በወር እንዲከፍላቸዉ የተወሰነዉ 20000 ብር ቀለብ አሁን ካለዉ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ይህ የቀለብ መጠን ሊሻሻል አይገባም በማለት የግራ ቀኙን አቤቱታዉ ዉድቅ በማድረግ አስቀድሞ የተወሰነዉን ቀለብ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር አመልካች ከሌላ ሚስት የወለዳቸዉ አምስት ልጆች ያላቸዉና እነርሱም ለኑሮ የሚያስፈልጋቸዉን የማሟላት ግዴታ ያለበት በመሆኑ፤ አመልካች ከዚህ ቀደም ሲሰራ የነበራዉን የሥራ ፈቃድ መመለሱ የተረጋገጠ ሲሆን አሁን ሥራዉን እየሰራ ነዉ የሚል ክርክር ያልቀረበ በመሆኑ፣ በኮሮና በሽታና በሌሎች ምክንያቶች በንግድ ሥራዉ ላይ መቀዛቀዝ መምጣቱ ተረጋገጠ በመሆኑ፣ የአሁን ተጠሪ ቀደም ሲል ቀለብ ሲወሰን የነበረባቸዉ የቤት ኪራይ ወጪ የቀረና ግራ ቀኙ በሽማግሌ ባደረጉት ስምምነት በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 በአሁን አመልካች ስም ተመዝግቦ በሚገኘዉ ፎቅ ቤት እየኖሩ በመሆናቸዉ፣ የአሁን አመልካች ከተጠሪ ከተወለዱ አራት ልጆች ጋር ዘጠኝ ልጆች ቀለብ የሚሰጥ በመሆኑ፣ ቀደም ሲል ቀለብ ለመወሰን ያበቁ ምክንያቶች የተለወጡ መሆናቸዉ የተረጋገጠ ስለሆነ የአሁን አመልካች ወር በገባ ከ25-30 ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ከመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም ብር 12000 (አስራ ሁለት ሺህ) ለልጆች ቀለብ እንዲከፍሉ በማለት በማሻሻል፤ እንዲሁም የአሁን አመልካች በተጠቀሰዉ ሕንጻ በ2ኛ ወይም በ3ኛ ወለል ላይ በንብረቱ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ እስከሚሰጥ እንዲኖሩ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ ዉሳኔ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትን ዉሳኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ በአመልካች ሥር የሚተዳደሩት በአጠቃላይ ከ20 በላይ ቤተሰብ በመሆኑ፣ የአመልካች ገቢም በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱ እና ንግድ ፈቃድን መመለሴ ያልተካደ የታመነ፣ አመልካች ከንግድ ሥራ አገኝ የነበረዉ ገቢ ሙሉ በሙሉ የቆመ መሆኑ ተረጋገጠ እያለ፤ ከሁለት ሚስቶች 12 ልጆች የወለድኩኝና ከፍተኛ የወጪ ጫና ያለብኝ፣ ቀለብ እንዲቆረጥላቸዉ የተወሰነላቸዉ ልጆቼ በአሁኑ ሰዓት የሚኖሩት እኔ በሰራሁት G+3 ሕንጻ ዉስጥ እየኖሩ ይገኛሉ፤ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የወሰነዉ ቀለብ ብር 12000 የወሰነዉ ተገቢ ሆኖ ሳለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወር ብር 20000 ቀለብ ለልጆች እንዲከፍል መወሰኑ፤ አመልካች የሚኖርበት ቤት የሌለኝ በመሆኑ ተጠሪ በራሷ ፍሎር ላይ የምትኖር ምንም የሚያገናኘን ነገር የሌለ ሆኖ ሳለ በአንድ ሕንጻ መኖር የለባቸዉም በማለት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፤በዚህ ጉዳይ አመልካች የንግድ ፈቃድ መመለሱ ያልተካደ ከመሆኑ አንጻር የተወሰነዉ ልጅ ቀለብ ገንዘብ መጠን አቅምና ገቢዉን ያገናዘበ መሆኑ አለመሆኑ ከፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 202 (2) ድንጋጌ አንጻር፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ22/11/2014 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ አመልካች የንግድ ፈቃድ ስለመመለስ የሚል ማስረጃ መሰረት በማድረግ ያቀረበዉ የቀለብ ይቀነስልኝ ጥያቄ ቀደም ሲል ያልቀረበና ለቀለብ አወሳሰን መነሻ ያልሆነ ነዉ፤ አመልካች ቀደም ሲል ቀለብ እንዲቀነስልኝ በማለት ያቀረበዉ ምክንያት ከመኪኖች ዉጭ ሌላ ገቢ የለኝም የሚል ሲሆን ይኼዉ ከግንዛቤ ገብቶ የልጅ ቀለብ ብር 20000 እንዲሆን ተወስኖለታል፡፡ አመልካች ቀለብ ሲወሰን የቁም እንስሳት ንግድ ፈቃድ መመለሱን የሚያመለክት ነገር ያልቀረበ በመሆኑ፤ አሁንም አመልካች የንግድ ፈቃድ በመመለሱ ምክንያት ገቢዉ መቀነሱን ያቀረበ ማስረጃም የለም፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በማጣራት የወሰኑት የልጆች ቀለብ በአግባቡ ስለሆነ እንዲጸናልኝ፤ በዚህ ክርክር ያወጣሁትን የወጪ ዝርዝር እንዳቀርብ መብት እንዲጠበቅልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ2/12/2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ከዚህ ቀደም ቀለብ ለመወሰን ምክንያት የሆነዉ ሁኔታ የተለወጠ በመሆኑ፣ የንግድ ፈቃድ በመመለስ የማገኘዉ ገቢ ስለቆማ ከተጠሪ እና ከሌላ ሚስት ለወለድኳቸዉ 12 ልጆች የተወሰነዉ ቀለብ ለመክፍል አቅም ስለሌለኝ እንዲቀነስልኝ በማለት የተከራከሩ ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩላቸዉ አመልካች ያቀረበዉ ክርክር ቀደም ሲል ቀለብ ሲወሰን ለዉሳኔዉ ምክንያት ያልሆነ መሆን ብቻ ሳይሆን በማስረጃም ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር ተገቢ ነዉ ያሉትን ዉሳኔ ማሳለፋቸዉን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ እንደሚታወቀዉ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰዉ እንደባለጉዳዮቹ ሁኔታና እንደአካባቢዉ ልምድ የሚስማማዉን በመከተል የቀለብ ተቀባዩ ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ፣ ጤናዉን የሚጠብቅበትና እንደሁኔታዉ ለትምህርት አስፈላጊ የሆነዉን ነገር መስጠት እንዳለበት የፌዴራሉ የተሻሻለዉ ቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 197 ሥር ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የቀለቡ መጠን የሚወሰነዉ ቀለብ ጠያቂዉ ያለበትን ችግር እና የቀለብ ሰጪዉን አቅም በመመዘን መሆን እንዳለበት በዚህ ሕግ አንቀጽ 202 (2) ሥር ተደንግጓል፡፡ የቀለብ መጠን በበቂ ምክንያት ማሻሻል እንዲሚቻልም በዚህ ሕግ አንቀጽ 203 ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ከተጠሪ ለተወለዱት አራት ልጆች በወር 20000 ብር ቀለብ እንዲከፍል ከተወሰነ በኋላ የተለወጡ ሁኔታዎች መኖራቸዉን የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች የነበረዉ ንግድ ፈቃድ የመለሱ መሆኑን፤ ከንግድ ስራዉ ሲያገኝ የነበረዉ ገቢ የቀነሰ መሆኑን፤ አመልካች ከሁለት ሚስቶች ለወለዳቸዉ ዘጠኝ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ልጆች ቀለብ የመክፍል ግዴታ እንዳለበት፣ ተጠሪ በአመልካች ስም ተመዝግቦ በሚገኝ ሕንጻ አንደኛ ወለል ላይ የሚኖሩ በመሆናቸዉ የኪራይ ወጪ የሌለባቸዉ መሆኑን፣ በአመልካች በኩል የቀረበዉ ክርክርና ማስረጃ መረጋገጡን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረበዉ ክርክር ሲታይ አመልካች የንግድ ፈቃድ የመለሰ መሆኑን አልካዱም፣ በዚህ ምክንያት ገቢ አልቀነሰም ይበሉ እንጂ አመልካች የንግድ ፈቃድ ከመለሰ በምን አግባብ ሥራዉን ሰርቶ ገቢ እንደሚያገኝ ያመለከቱት ነገር የለም፣ እንዲሁም አመልካች እየሰራ የሚያገኘዉን የገቢ መጠን በተጨባጭ በማስረጃ አስደግፈዉ ያመለከቱት ነገር የለም፣ ተጠሪ ቀደም ሲል የቤት ኪራይ ወጪ የነበረባቸዉ ቢሆንም አሁን በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉ ሕንጻ አንደኛ ወለል ላይ እንደሚኖሩ አልካዱም፣ እንዲሁም አመልካች ከሌላ ሚስት ለወለዱት አምስት ልጆች የሚያስተዳደሩ መሆናቸዉን አልካዱም፡፡ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ የጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የጠየቀሳቸዉ ምክንያቶች በማስረጃ አልተረጋገጡም፣ አመልካች አሁንም በቂ ገቢ ያገኛሉ በማለት በማስረጃ ያረጋገጡ ፍሬ ነገር መኖሩን ያመለከቱት ነገር የለም፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ቀደም ሲል ቀለብ ሲወሰን የነበረዉ የአመልካች ሁኔታ እና ልጆች የሚኖሩበት ሁኔታ መቀየሩን የሚያመለክት በመሆኑ፣ በተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 203 የቀለቡን መጠን ለማሻሻል በቂ ምክንያት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የተለወጠ ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት አመልካች በየወሩ ብር 12000 ከተጠሪ ለወለዷቸዉ ልጆች ቀለብ እንዲከፍሉ የወሰነዉ በሕጉ አግባብ ነው ነገር ግን የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የጠቅላይ ፍ/ቤት ያሳለፉት የቀለብ መጠን ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ቀደም ሲል የልጆች ቀለብ ሲወሰን ተጠሪ ቤት ተከራይተዉ ልጆቹን የሚኖሩአቸዉ በመሆኑ፣ ግራ ቀኙ በሽማግሌ በኩል ባደረጉት ስምምነት ተጠሪ ልጆቹን ይዘዉ በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ዉስጥ የሚገኘዉ G+3 ላይ በአንደኛ ወለል ላይ እንዲኖሩ በተስማሙት መሰረት በዚህ አግባብ ተጠሪ ከልጆቹ ጋር በዚህ ቤት እንደሚኖሩ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክርክር ይህን ጉዳይ በሽምግልና የተስማሙ በመሆኑ አሁን ሊነሳ አይገባም ከማለት ባለፈ በሽማግሌ ስምምነቱም ሆነ በፍ/ቤት ትዕዛዝ አመልካች እዚህ ቤት እንዳይደርስና በየትኛዉም ክፍል ዉስጥ እንዳይኖር መወሰኑን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ ከልጆቻቸዉ ጋር በአንደኛ ወለል ላይ የሚኖሩ እስከሆነ ድረስ፣ አመልካች በ2ኛ ወይም በ3ኛ ወለል ላይ ቢኖር በተጨባጭ የሚፈጠር ችግር መኖሩን ከወዲሁ ለመናገር አስቸጋሪ ነዉ፡፡ አመልካች በዚህ ሕንጻ በ2ኛ ወይም በ3ኛ ወለል ላይ በመኖር በተጠሪ ላይ የሚፈጥረዉ ችግር ካለ የአሁንተጠሪ ይህን ሁኔታ ለፍ/ቤት በማመልከት ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ ከቤቱ እንዲለቁ ማስደረግ የሚከለክላቸዉ ነገር የለም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ሕንጻዉ ዘንድ እንዳይደርስ እንዳይኖር በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡
ሲጠቃለል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ሁኔታ መለወጡን በማረጋገጥ አመልካች እንዲከፍል የተወሰነዉ የቀለብ መጠን በማሻሻል ያሳለፈዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ ሳለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀለብ መጠን ለማሻሻል በቂ ምክንያት የለም በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.104085 በ6/5/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.224577 በ23/10/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.286991 በ30/7/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡
የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት
አ/ኃ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም